Attention to Kebede (PCA)

3.4.2/45/2

18 ህዳር 2004

... ፌዴ...ዊ ... ሪፐብሊ...
... ...ልጣን
...public

Ethiopian ... and Customs Authority

ለአዲስ አበባ ንግድ ዕ/ማ/ቅ/ጽ/ቤት

ጉዳዩ፡- የኮንስትራክሽን ማሽነሪ አከራዮች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገቧቸው ፒክ-አፕ ተሽከርካሪዎች የቀረጥና ታክስ አከፋፈልን ይመለከታል፡-

በቁጥር አንዕ70/ደ43/96 በ08/02/04 ለዳይሬክቶሬታችን በተፃፈ ደብዳቤ በኮንስትራክሽን ማሽነሪ አከራዮች የኢንቨስትመንት ዘርፍ በተመለከተ በኦዲት ስለተጠየቀ ተጨማሪ ሂሳብ አከፋፈል ሁኔታ የህግ አስተያየት የጠቃችሁን መሆኑ ይታወሳል።

በዚህም መሠረት የድህረ-ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ቡድን ለህግ ምክርና ማሻሻያ ቡድን ማብራሪያ እንዲሰጥበት ተጠይቆ ዝርዝር አፈፃፀሙን በተመለከተ በቁጥር ህ/ም/ማ 170/2004 በ13/03/04 ምላሽ ተሰጥቶበታል። ስለዚህ የተሰጠውን አስተያየት ከዚህ ደብዳቤ ጋር 2 ገጽ አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal ... Republic of Ethi... Revenues and Customs Authority

ታለሕይወት መኮንን
የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት አሠራር ፕሮግራም ልማት ቡድን አስተባባሪ

ግልባጭ፡-

- ለታክስ ኦዲት አሰራር ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
  የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

Ethiopian Revenue and Custom Authority

የውስጥ መፃፃፊያ

Inter-office Memo

---

ለ፣ ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት አሰራርና ፕ/ል/ቡድን　　　　ቀን፣ 13/03/04

ከ፣ ህግ ምክርና ማሻሻያ ቡድን　　　　ቁጥር፣ ሕ/ም/ማ/70/2004

ጉዳዩ፣ <u>ከቀረጥ ነፃ የገባ ተሽከርካሪ ቀረጥና ታክስ የሚሰላበት ጊዜን በተመለከተ</u>

<u>የጉዳዩ ፍሬ ነገር</u>

የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ ለኮንስትራክሽን ማሽነሪ አከራዮች አዋጅን፣ ደንብን እና መመሪያን በተፃረረ መልኩ ፒክ አፕ ተሽከርካሪ ተፈቅዶ በመገኘቱ የቀረጥ ነፃ መብታቸው ተነስቶ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ባለሀብቶች መጠየቃቸውን እንዲሁም የቀረጥና ታክስ ክፍያ ጥያቄ አሁን ባለው የምንዛሪ መጣን በመሆኑ ክፍያው ከፍተኛ እንዲሆን በማድረጉ ይህንንም አሠራር ባለሀብቶችም በመቃወም ቀረጥና ታክስ መክፈል ካለባቸው ተሽከርካሪው በገባበት ጊዜ በነበረው የምንዛሪ ምጣኔ መሠረት መሆን አለበት በማለት አቤቱታ ለቅ/ጽ/ቤቱ ማቅረባቸውን ገልፃችሁ የተሽከርካሪዎች ቀረጥና ታክስ አከፋፈል ጋር በተያያዘ ተሽከርካሪዎቹ በገቡበት ወቅት በነበረው ወይም አሁን ባለው የምንዛሪ ምጣኔና የቀረጥና ታክስ ዓይነቶች በየትኛው መሠራት እንዳለበት፤ በቀን 16/02/2004 በተፃፈ ደብዳቤ አስተያየት መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡

<u>ጭብጥ</u>

የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የሚወሰንበት እና የዋጋ ማስከፈያ የገንዘብ ምንዛሪ ልክ የሚሰላበት ጊዜ መቼ ነው?

<u>አግባብነት ያላቸው ህጎች</u>

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 65(1)

## የህግ አስተያየት

ወደ አገር ሰገባ ወይም ከአገር ሰወጣ ዕቃ የተከፈለው የጉምሪክ ቀረጥና ታክስ በማናቸውም ምክንያት ሲከፈል ከሚገባው ያነሰ መሆኑ በምርመራ የተደረሰበት እንደሆነ ባለሥልጣኑ የዕቃውን ባለቤት ወይም ወኪሉን በልዩነት ያልተከፈለውን ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ጉድሉ ከቀረበት ቀን ጀምሮ በአሥር ዓመት ጊዜ ውስጥ ሊያስከፍል እንደሚችል በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 65(1) ላይ የተገለፀ ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ፍተሻ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር የገቡ ተሽከርካሪዎተ እንዳሉ በምርመራ የተደረሰበት በመሆኑና በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የተገኘ ተሽከርካሪ ሲከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ያነስ ሲሆን ሊከፈል የሚገባውን የቀረውን ቀረጥና ታክስ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሊያስከፍል እንደሚችል ነው።

በመሆኑም ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ገብተው የተገኙ ተሽከርካሪዎች ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ዕቃው ሲገባ በነበረው ምንዛሪ ቀረጥና ታክስ እንዲከፈል ቢደረግ የተሻለ ነው በማለት ያለንን አስተያየት እናጠናቅቃለን።

ከሰላምታ ጋር